የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.24
ADDIS ABABA, 8th April, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፭/፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ……………ገጽ ፲፫ሺ፪፻፳፪

## Content

Proclamation No. 1245/2021

Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Uganda Ratification Proclamation……………………………………..page13222

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፭/፪ሺ፲፫

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በካምፓላ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱን ማጽደቅ በወንጀል ምርመራና ክስ ሂደት መረጃና ማስረጃዎችን ለማግኘት እንዲሁም በወንጀል የተገኙ ወይም ወንጀል ለመፈፀም አገልግሎት ላይ የዋሉ ንብረቶችን ለመያዝ፣ ለማገድና ለመውረስ የሚደረግ በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብርን የሚያበረታታ እና የሚያጠናክር በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1245 /2021

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE MUTUAL LEGAL ASSISTANCE IN CRIMINAL MATTERS AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF UGANDA

**WHEREAS,** the Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement between the government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and the government of Republic of Uganda has been signed in Kampala, on the 16th day of August 2019;

**WHEREAS,** ratifying the Agreement promotes and strengthens international cooperation in criminal matters to obtain information and evidence in the investigation and prosecution of offences as well as in seizing, freezing and confiscation of proceeds or instrumentalities of crime;

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ባካሄደው ፲፪ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፭/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በካምፓላ የተፈረመው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከሌሎች ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን የማስፈጸም ስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

**WHEREAS**, the House of Peoples'Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Mutual Legal Assistance Agreement at its 12th Regular session held on 24th day of March, 2021,

**NOW,THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement between the governmet of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the government of Republic of Uganda Ratification Proclamation No.1245/2021".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement signed in Kampala on the 16th day of August, 2019 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Uganda is hereby ratified.

**3. <u>Responsibility of the Attorney General</u>**

The Attorney General of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby authorized to follow up the implementation of the Agreement in collaboration with other relevant government organs.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force up on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 8th Day of April,2021**

**SAHLEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**